# ለአዚው አገር መንገደኛ ለአቶ ኤፍሬም የምላቸው አለኝ።

May 24, 2017 14:42

ከደምሳቸው ንጋቱ



ኤፍሬም ማዴቦ

የመንገደኛው ጋዜጠኛን መሰሉ የአቶ ማዴቦን ጽሁፍ በወርድ በቁመቱ ወረድኩበት።የአዚን አገር ከእግር እስከራሱ እንደሄዱበት ነገሩን። ያጻጻፋቸው ይትባህልና አጀማመር ሊሰነዝሩልን የፈለጉት መልእክት ማዋዣነት የተጠቀሙበት ስለመሆኑ ማሳበቁ አልቀረም። እርግጥ ነው ሊሰብኩን ለተነሱበት ጭብጥም ስለአዚ የጠቃቀሱት በማጠናከሪያነት የረዳቸው አይመስልም። ስለአዚ መልከአምድርና የትዬለሌነቷን ከሚነግሩን የተሻለ ሊሉት የሚገባውና በፓለቲካውም ሊያግዛቸው ይችል የነበረ ጉዳይ አለ ። አውስትራሊያ የመድብለ ባህል /MULTICULTURALISM/ የተሳካባት ቁንጮ ምእራባዊ አገር ነች ። የሕግ የበላይነት የሰፈነባት፤ የሰዎች ባህል ቋንቋና እምነት የተከበረባት የተለያዩ ብሄረሰቦችን ቁጥር ሳይጨምር ከ 224 አገሮች በላይ ዜጎች ተከባብረውና በጋራ የሕግ ጥላ ሥር የሚኖሮባት እድልኛ አገር በመባል ትታወቃለች። ብዙም ብዙም በጋራ የመኖርን ፋይዳና አንድነትን ለማጉላት የሚበጅ ታሪክ ያላት አገር ነች። ስለመጀመሪያዎቹ የእንግሊዝ ሰፋሪዎች ከሚያወሱልን ይልቅ ይሄ ሚዛን ይደፋ ነበር ለማለት ነው። ጽሆፎ ከአዚ አገር ስለተነሳ እኔም ከዚያው ልጀምር ብዬ ነው።

አቶ ኤፍሬም ለመሆኑ «በመስታወት ቤት ውስጥ የተከበበ ሰው ድንጋይ ለመወርወር የመጀመሪያ መሆን የለበትምን» ሰምተው አያውቁም። ለመሆኑ የአእምሮ በሽታ ማለት ምን ይሆን? መገለጫዎቹ ምንድናቸው? ደግሞስ « አትግደሉኝ፤ካገሬ አታፈናቅሉኝ» ያለ አማራ እራሱን ሊከላከል ቢደራጅ እርሶን ለምን ሆዶን ቆረጠት። አዩ የእርሶ ድርጅት አሁንም ወረቀት ከመበተን እንኳን አላለፈም። ብዙዎቻችን የእርሶን ድርጅት ተስፋ አድርገን በምንችለው አቅም ረዳን ። የተፈጠረላችሁን መልከማ አጋጣሚ አለመጠመቀማችሁ ብቻ ሳይሆን ስንት የስልት ግድፈት ፈጸማችሁ። የአንድነት ሃይሎች ቢሳካላቸው አማራው ይጠላል የሚል የተዛባ አመለካከት አሎት ብዬ ለመገመት ያዳግተኛል። ለዚህም ሲባል አማራው ከጥንት እስከዛሬ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሏል። ይሁን እንጂ በእናንተ በኩል እንኳን ቆሞ የሚሄድ ዳዴ የሚል ነገር እንኳን ማየት ህልም ሆነ። ስለሆነም የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም ሆነና አማራው ያልሞት ባይ ተጋዳይ ትግል ጀመረ። ይሄ ደግሞ እሰየው ያሰኛል እንጂ ለአካኪ ዘራፍ ምክኒያት አይሆንም። ምክኒያቱም አማራው ባንዲራው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ አገሩ አንድ ኢትዮጵያ መሆኗን ሙጥኝ ያለ ከዚህ ውጭ በምንም የማይጠረጠር ሕዝብ ነው።

ደጋጎቹና ጨዋዎቹ የአማራ ዘመዶቼ የኑሮ መመሪያ ሲሰጡኝ እንዲህ ነበር ያሉት« ሰውን አልፈህ ተርፈህ ሙብቱንና ማንነቱን አትጋፋ። ማንም ይሁን ማን አክብር ። ካለህ ላይ ለማካፈል አትቦዝን። ድንበር አልፎ አሻፈረኝ ብሎ እምቦር እምቦር ያለ እንደሆን ግን በለው ነበር።» ያሉኝ። አያይዘውም ከባለጌ ጋር እሰጣ ገባ ውስጥ አትግባ ምክኒያቱም ወደ እሱ ደረጃ ትወርዳለህና» አስተያየቴ ከዚህ መርህ ጋር እጅና ጓንት እንዲሆን የተቻለኝን ጥንቃቄ ወስጃለሁ።

አቶ ኤፍሬም እናንተ እኮ አማራው ሲፈናቀል ሲጨፈጨፍ አንድ ጠንከር ያለ መግለጫ እንኳን እኮ ነው የነፈጋችሁት። ለምን?« ከቀድሞው ጨቋኝ » ጋር አበራችሁ እንዳትባሉ የፓለቲካ ስልት ብጤ መሆኑ ነው። ከእናንተ ይልቅ የጀነራል ከማል ገልቹ ድርጅት የአማራውን ከጉራፈርዳ መፈናቀል በተመለከተ ለአብነት የሚጠቀስ ጠብሰቅ ያለ መግለጫ አውጥቷል።

ብዙ ጊዜ ድርጅቶዎ ከሚመልሳቸው ጥያቄዎች ይልቅ የሚፈጥረው ጥያቄ ይበልጣል። የምትፈጽሙት ያሰራርና የፓለቲካ ስህተት ደግሞ እጅግ ብዙ ነው። ለመሆኑ ለምታደርጉት ነገር ፓሊሲና መመሪያ የሚባል ነገር አላችሁ ወይንስ እንደመጣላችሁ ነው የምትሰሩት? ይሄን ያልኩት ያለምክኒያት አይደለም። ለምሳሌ የአቶ አንዳርጋቸው ወያኔ እጅ ውስጥ መውደቅና በወቅቱ አድበስብሳችሁ ያለፋችሁት ጉዳይ ምን ያህል እርጥብ ፓለቲከኞች መሆናችሁን የሚያሳብቅ ጉዳይ ነው። የድርጅታችሁን ቁንጮ መሪ በወቅቱ ከሁላችሁም የተሻለ ይንቀሳቀሱ የነበሩትን ሰው በየመን ተጉዘው ለትግሬ ወያኔ ገጸበረከት አደረጋችሃቸው። እራሳችሁን የማትጠብቁ

እንዴት ለሌላው ትተርፋላችሁ?አቶ አበበ ገላው በቅርቡ በከተበው የእንጊሊዝኛ መጣጥፉ ላይ በአቶ አበበ ቦጋለና በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ መካከል በየመን በኩል መሄድና አለመሄድን አስመልክቶ  ሃሳብ ተለዋውጠው እንደነበር አስነብቦናል። ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘም የወያኔዎች አንዱ ቱባ ባለስልጣንና አሁን የአለም አቀፍየጤና ድርጅት ዳይሬክተር የሆነው ሲሳለቅባችሁ « እንዴት እሳቸው(አቶ አንዳርጋቸውን ማለቱ ነው)የደህንነት መ/ቤታችን እንደሚከታተላቸው እያወቁ አለመጠንቀቃቸው ይገርማል» ማለቱም ይታወሳል። ለመሆኑ የመሪዎቻችሁን ደህንነትና እንቅስቃሴ የሚገዛ ፓሊሲና ለድርድር የማይቀርብ መመሪያ የላችሁም? ወይንስ ግለሰቦች በየፊናቻው ነው ያሻቸውን የሚያደርጉት? አቶ አንዳርጋቸው በተያዙ ሰሞንም እጅ እግር የሌለው መግለጫ የሰጡትም የኦዚው አገር ጎብኚ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ እርሶ ነበሩ።

ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅምና እርሶዎ በተለያየ አጋጣሚ አማራውን ለመተናኮል አለመቦዘኖን የሚያሳይ ብዙ የጽሁፍ መረጃ አስቀርተውልናል። ለነገሩማ ሃጼ ምኒሊክንም ተችተዋል። ሞት ሰውን ሁሉ እኩል ያደርጋል አሉ። ምኒሊክ በአቶ ኤፍሬም አፍ መተቸታቸው  ይገርማል።

ሳይቸግሮት ተናግረው እኔንም አናገሩኝ። የቤት ስራዎንም በደንብ ሳይሰሩ ቀርተው በእርሶ ቤት ጥቂት አማሮች ብቻ ውርውር የሚሉ አስመስለው ለማቅረብም ሞክረዋል። አዩ አማሮች ታጋሾች እንጂ ተላላዎች አይደሉም። እንዴት አብረውት የኖሩትን  ሕዝብ እንኳን በቅጡ አያውቁም። ይታዮት  ነገሮች ምን ያህል እያመለጧችሁ እንደሄዱ? እንኳን ሁኔታዎች ላይ ተጽእኖ ልታሳርፉ ይቅርና ክስተቶችን ለመረዳት እንኳን አቅም እንዳጣችሁ ያሳያል።

እንቆቅልሹ እንገነጠላለን ፤ኢትዮጵያ ለ እኛ ምናችን ነች ወዘተ ከሚሉት ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ከወያኔ ጋር ህግ ካረቀቁት የነ ሌንጮ ድርጅት ኦነግና ኦብነግ እና መሰል ድርጅቶች  ጋር ግንባር እንፍጠር እያላችሁ እየተፋራረማችሁ ስታበቁ አማራን ማውገዛችሁ የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንደተባለላት ሴት ሆናችሁ። አዎ አማራ የእናንተ ባጣ ቆየኝ አይደል።

ነገሬን ከእርሶ ጋር ገና አልቋጨሁም።  በናንተ የስልት ጉድለትና ጉራ ወይም ዲሲፕሊን እጦት በተለይ የድርጅቶ መሪ «ወያኔን የምናሸንፈው እዚያው ጉያው ሥር ሆነን» ነው እያለ ባንድ ወቅት ደጋግሞ መግለጫ በመስጠትና ለወያኔዎች ፍንጭ በመስጠት  በመንግስት ግልበጣ ስም ትግሉን ዛሬ ለማጦዝ ይረዱ የነበሩ የአማራ ከፍተኛ የጦር መኮንኖችን እስር ቤት እንዲማቅቁ ያደረጋችሁ እናንተ አይደላችሁም? ወጣቷ ንግስት ይርጋ «አማራ አሸባሪ አይደለም» የሚል ካናቴራ ለብሳ በመውጣቷ በእናንተ ድርጅት ስም አይደል የተከሰሰችው?  እረ ስንቱን ልጥቀስ። ተግባር አልባ በሆነው ስማችሁ ብቻ ስንቱን ለክፉ ቀን የሚሆን ታጋይ በተለይ አማራ አስለቀማችሁት።

ከሁሉ የሚገርመው ለእናቷ ምጥ አስተማረች እንዲሉ አቶ ኤፍሬም ለአማራው ስለአንድነትና ስለኢትዮጵያዊነት ለመስበክ መሞከራቸው ነው። ነገሩ ወዲህ ነው እናንተ በኢትዮጵያ ስም ከላይ ሆናችሁ ልትዘውሩ አማራው የእናንተ ጠመንጃ አንጋች ሊሆንላችሁ ሞኛችሁን ፈልጉ!ከሁሉም ግራ የሚገባው ለጣሊያኖች ወይም ለአረቦች የምትሰብኩ  ይመስል በኢትዮጵያዊነት ነው መሰባሰብ የምትሉት ቋንቋ ነው። ወያኔዎች ኢትዮጵያን በዘር ሸንሽነው አንዱን ባንዱ ላይ እያዘመቱ በተለይም አማራውን ኢላማ አድርገው ሲፈጁት የአንድነት ሀይል የሚባል በሌለበት ምድር እጁን አጣምሮ ይለቅ ብላችሁ ነው ክርክራችሁ። ወይንስ እናንተ ሃይል እስክትፈጥሩ  ጦር እስክታደራጁ ሌላ 26 አመታት ቢፈጅም ጠብቁን ነው ሙግታችሁ። የትኛው ቋንቋ ነው ያልገባችሁ ? አማራው ያልሞት ባይ ተጋዳይነት መብት አለው እራሱን ለመከላከልም ብቃት አለው ስትባሉ ለምን ያዙኝ ልቀቅን ትላላችሁ?

እርሶ መቼም ጉደኛ ኖት! የትልቅነት ትምክህትም ተጠናውቷችሃል ነገር ነው ያሉት? አዩ የገጠጠውን ገሃድ መካድ ነው የጤና ማጣት ምልክት። ለመሆኑ ሕዝብ ብዛት የኢኮኖሚ፤ የመከላከያና የፈጠራ አቅም ሊያዳጉስ እንደሚችል ለመረዳት ልዩ ጠበብት መሆንን ይጠይቃል? በየትኛው ቀመር ሲሰላ ነው 2 ሚሊዮንና 40 ሚሊዮን ሰዎች ቢያንስ የሚያመርቱት እኩል የሚሆነው? ይሄ እኮ የስሜት ጉዳይ ሳይሆን የሚዳሰስ የሚጨበጥ እውነታ ነው።

ምንም ውስጥ የሌሉበት አፈር ገፊ አማሮች በዘረኞች ጥይት ሲታጨዱ። አለም በቃኝ ብለው የመነኑ መነኩሳት አይናቸው እየታሰረ ገደል ሲጣሉ። ለአመታት ያፈሩትን ንብረት ባንድ ሌሊት ተነጥቀው እንዳልባሌ ሲባረሩ  ቆርቁሮን ብንነሳና «እህት ወንድሞቻችን አትንኩ በአገራቸው በሰላም ይኑሩ» ብለን ድምጻችንን ብናሰማ የእእምሮ በሽተኛ ብለው ጳያፍ ስድብ ለምን ይሳደባሉ?   ወያኔ እኮ ያጠቃው ሌላውንም ብሄረሰብ ማለትም አማራውንም ፤ከንባታውንም፤ጉራጌውንም ኦሮሞውንም ነው ይባል ይሆናል። አማራው በተጎዳበት መጠንና አይነት ግን ማንም ላይ አልደረሰም። ይሄ ደግሞ አሉባልታ ሳይሆን በጥናት የተደገፈ በአሃዝና በአይነት የተመዘገበ በዳጎሰ መድብል የተጠረዘ መረጃ ያለው ጉዳይ ነው።

በኢትዮጵያዊነት እንደሚሉን የሚቆረቆሩ ቢሆንማ ኖሮ በአማራው ላይ ወንጀል ሲፈጸም «ወንድም እህቶቻችንን አትንኩ በክፉም በደጉም አብረን የኖርን ነን። ጥቃታቸው ጥቃታችን ነው» ብለው ከፊት ቀድሞው ሌላውን ኢትዮጵያዊ አስተባብረው የበሰለ ስራ አሳይተውን ቢሆን ኖሮ እራስን ለማዳን ወደ ተፈጥሯዊ ትግል ባላመራንም ነበር። ሞታችን ሞታችሁ ካልሆነ ስቃያችን ስቃያችሁ ካልሆነ የራሳችንን ችግር በራሳችን ከመጋፈጥ ውጭ ምን አማራጭ አለን?

ከእርሶ አጻጻፍ ምንም ሊጨበጥልኝ ያልቻለው ሌላው ሃሳብ «የእኔ የግሌ አስተያየት» የሚለው ሃረግ ነው። አቶ ኤፍሬም አርበኛ ሆነው ወደ አዚ አገር ባይሄዱና ቱሪስት ሆነው ሄደው ቢሆን ኖሮ የጻፉት የእኔንም ጊዜና የብእር ቀለሜን ይቆጥብልኝ ነበር።

የአማራውን መደራጀት ጉዳይ ለአማራው ቢተውለት ለርሶም ስራዎን ያቀልሎታል። በሌላ በኩልም የሚያነቡት መጽሃፍ ቅዱስም «አትፍረድ ይፈረድብሃል» ይል የለ።